“መሠረቶቿ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው።”(መዝ፤86፥1)

## ጽዮን ተወለደች

የኢያቄምንና የሐናን
ልመና ጸሎታቸውን ሰምቶ
ያማቸውን ተቀብሎ
ዕንባቸውን አብሶ
ደስ አሰኛቸው አምላክ ባርኮ
ለእናትነት የመረጣትን ሰጥቶ።
ከፀሐይ ከጨረቃ ይልቅ ልቃ
ከፍ ብላ አምራ ደምቃ
ከኪሩቤል የምትበልጠው
ከሱራፌል የምትልቀው
የተጌጠች በቅድስና
የተለየች በንፅሕና
ሐመረ ኖህ ምክንያተ ድሂን
የአዳም ተስፋው
ተወለደች ድንግል ደስ ይበላችሁ።
ዕልልታው ያስተጋባ
ከበሮው ይመታ
ይሰማ ድምፃችሁ በከፍታ
ሰጥታናለችና ልዩ ደስታ
እነሆ ድንግል ዛሬ በመወለዷ።
ሐርና ወርቅ እያስማማች
የምትፈትል ድንቅ አማላጅ
ለዓለም ድህነት ለሚመጣው
ለክርስቶስ ማደሪያው
ተወለደች እመቤታችን ደስ ይበላችሁ
የአዳም ልጆች ሁላችሁ
አመስግኑ በዕልልታ
ይሰማ ድምፃችሁ በከፍታ።
የፃድቃን እመቤታቸው
የሰማዕታት እናታቸው
የመላዕክት እኅታቸው
የነቢያት ትንቢታቸው
የሐዋርያት ሞገስ ስብከታቸው
ተወለደች ድንግል ደስ ይበላችሁ።
የዘላለም ማረፊያው
የእግዚአብሔር ከተማው

የመረጣት ማደሪያው
ጽዮን ዛሬ ተወለደች
ደስ ይበልህ ኢያቄም የዳዊት ወገን
ደስ ይበልሽ ሐና የአሮን ወገን
ደስ ይበላችሁ የእመቤቴ ልጆች
አመስግኑ በዕልልታ
ይሰማ ድምፃችሁ በከፍታ
አሸብሽቡላት ለእመቤቴ
ዘምሩላት ለእናቴ
ሰጥታናለችና ልዩ ደስታ
እነሆ ዛሬ በመወለዷ።
ዕልልታው ያስተጋባ
ለምሥራቅ በር ለኪዳኗ
እንደ ሰዶም እንደገሞራ
በእሳት ነደን እንዳንጠፋ
ሐዘናችን እንዳይበዛ
በዲያብሎስ ስር እንዳንገዛ
ሰጠን ንፁህ ዘር አስቀርቶ
ከተመረጡ የተመረጠች አድርጎ
ልዑል ማደሪያውን ቀድሶ
ከኢያቄም አብራክ ከሐና ማህፀን ከፍሎ
ተወለደች ድንግል ደስ ይበላችሁ
አመስግኑ በዕልልታ
ይሰማ ድምፃችሁ በከፍታ
አሸብሽቡላት ለእመቤቴ
ዘምሩላት ለእናቴ
ሰጥታናለችና ልዩ ደስታ
እነሆ ድንግል ዛሬ በመወለዷ።

ከኃይለመስቀል ተስፋዬ
ለንደን(06/2002/ዓ/ም)